# እሪ ! በይ ኢትዮጵያ !!!







[ቁጥር ፪(2)][*1]

እሪ ! በይ እማማ ኢትዮጵያ - ካንጀትሽ አምርረሽ አልቅሽ፣
በወርቃማ ብዕሩ እሚስልሽ - ከልቡ ሽሽጎ እሚወድሽ፣
በስስት ዐይኑ እሚያይሽ - የሕይወት ሙሉ ጠበቃሽ፣
ብላቴን ጌታ ጸጋዬሽ መጣልሽ ከሩቅ ተጉዞ ሊሰናበትሽ።

**ይወጣልሽ ይሆን ጸጸቱ ?**
**የቁም ሰቆቃ ሃፍረቱ ?**

እሱማ ሁሌም ባንቺ ምሎ - አንጀቱን አስሮ በህመሙ፣
ያንቺኑ ህመም ሕፀጽ ሲያክም - ሲከትብሽ በቀለሙ፤
ሌት - ተቀን እንዳማጠ - ትንሣኤሽን እንደተመኘ፣
ከቶ መላ ሳይገኝልሽ - ወደ ዘላለም ቤቱ ተሸኘ።

እስኪ ይሁን እንግዲህ - የቋጠሮሽን ውል ጊዜ እስኪፈታው፣
ከጥቁር አፈርሽ እቅፍ - ፍቅርሽን ሊሻ ለመጣው፣
ለጀግናው ልጅሽ ለጸጋሽ - ካንቺው ለማይላቀቀው፣
የወርቅ ሐውልት ባይሆንልሽ - ጥርኝ አፈር አትንፈጊው።

እሱማ ተገላገለ ላንቺ እንጂ ወዮልሽ እማማ፣
ሰርክ ለምትዳክሪው ድንብርሽን በጨለማ፤
መከራሽ ለማይገታው - ሃዘንሽ ለማይሽረው፣
ልጆችሽን እየገበርሽ ከእዬዬ ላልተላቀቅሽው፤
ላንቺ ነው ለቅሶ እሚያስፈልገው፣
«አንቺ ነሽ እምባ እምትሺ[ው].......»[*2]!

« አንቺ እማማ ኢትዮጵያ አንቺ እናት ዓለም ... »[*3]
በፍቅር አቆላምጦ በዜማ ድምጸት ጥሪ፣
የሚሰይምሽ ጀግናሽን የበኩር ልጅሽን ሳታከብሪ፤
ቃሉ ይፈጸም ዘንድ ነብይ ባገሩ ላይከበር፣
ዳግም እንደነ ገብረክርስቶስ፥ ከበደ፥ አቤ፥ በዓሉ ...
ራእይ፥ ውጥኑ ...... ሳይደርስ ከዳር፤
አንድ ጎጆ በውል ነፍገሽው፣
« ሩቅ አሳቢ .... ቅርብ አዳሪ .... »[*4] ያረግሽው፣
«አንቺ ነሽ እምባ እምትሺ[ው].......»[*5]!

እርሱ ግን ራሱን ረስቶ፣
መላ ሕይወቱን ላንቺ ሰጥቶ፤
ቴዎድሮስ፥ ገብርዬሽን .....
ባልቻ አባነፍሶ፥ ጴጥሮስ፥ አሉላሽን ....
ለህልውናሽ የወደቁትን ከትቢያ እያነሳ ነፍስ ዘርቶባቸው፣
ጀግኖችሽን እየቀረጸ ለታሪክ ለትውልድ ያሳለፈው፤
የተተበተበ ቋጠሮሽን በብዕሩ ውል እየፈታ፣
ለአንድነትሽ ጽናት እማይዘነጋ ክቡር ውለታ..........
የዋለልሽ ብላቴን ጌታ !!!

... ሕይወቱን ሙሉ የጣረልሽን ይህን ታላቅ ጉምቱ፣
ባልንጀሮቹ እንኳ እንዳይሸኙት ወደ ዘላለም ዕረፍቱ፤
በወህኒ አጉረሽ ይዘሽ - ገሚሱንም ካገር አሳደሽ፣
የእንባ ስንቅ እንኳ ትነፍጊው ? የስሜት መግለጫ ፈሳሽ ?!
ሕዝቡም ጀግናውን እንዳይሸኝ - ሃገር ምድሩን በታንክ አጥረሽ፣
በብረት - ለበስ፥ ብረት ልቦች በሰው ነፍሰ - ገዳዮች ሞልተሽ .......

... እስኪ ይሁን እንግዲህ የቋጠሮሽን ውል ጊዜ እስኪፈታው፣
ከጥቁር አፈርሽ እቅፍ ፍቅርሽን ሊሻ ለመጣው፣
ለጀግናው ልጅሽ ለጸጋሽ ካንቺው ለማይላቀቀው፣
የወርቅ ሐውልት ባይሆንልሽ ጥርኝ አፈር አትንፈጊው።
እኔስ ተጨንቄ ነበር አፈርሽንም ትነፍጊው ይሆን ብዬ፣
ያንቺ ጉድ አያልቅምና «የጉዶች» ሃገር እምዬ።

... ተመስገን ነው ብቻ አንዳንዴስ - ይህንንስ ማን አየብን፣
ዛሬንም መድረሱን በተፀምር - ተመስገን ነው ላቆየልን፤
የመጣው የሄደው ሲያበግነው - አንጀት ኩላሊቱን ... ሲያሳርረው፣
በእሥር ... በድንጋይ ... ሲፈትነው - በመርዝ ሊገላገል ሲሞክረው፣
ያንን ሁሉ ... ጉድ አሳልፎም ለክብር - ኩራታችን ላበቃው፤
ተመስገን ነው ተመስገን ! ነብሱን በሠላም ያሳርፍልን !!!
እስመ - ለዓለም ምህረቱ ለዘለዓለም ዓለም አሜን !!!

☞ *1 - እሪ በይ ኢትዮጵያ ቁጥር - 1 ለፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ስንብት የተጻፈውን ግጥም ይመለከታል።
☞ *2, *3, *4, *5 - ከሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን እሳት ወይ አበባ የስነ - ግጥም መጽሀፍ የተጠቀሱ ናቸው።

ጌታቸው አበራ
የካቲት 23 ቀን 1998 ዓ.ም. ( ፳፫ - ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.)